# <u>ራስን መደገፍ አለመቻል፣ መገለል እና ግንኙነት፡ በ Covid19 መዘጋት ወቅት ለጥገኞች ድጋፍ</u>

የስኮቲሽ የጥገኞች ካውንስል ጥገኝነት ለሚፈልጉ ሰዎች እገዛ የሚሰጥ ገለልተኛ በጎ አድራጊ ነው።

ሰዎች ህይወታቸውን እንደገና መመስረት እንዲችሉ የሚታይ እገዛ እና በእያንዳንዱ የጥገኝነት ሂደት ላይ ተሰሚነትን እንሰጣለን። የሰዎች ህይወት ላይ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት ከማህበረሰቦች እና የማህበረሰብ ቡድኖች ጋር እንሰራለን እና የፖሊሲ ለውጦች እንዲመጡ ቅስቀሳ እናደርጋለን።

አብረን የምንሰራቸው ሰዎች በጣም ከባድ ከሆነ ሁኔታ ውስጥ የመጡ እና ግጭት እና ሰብአዊ መብት ጥሰት ከበዛበት ሃገር የመጡ ናቸው።

ሰዎች ስኮትላንድ ውስጥ ሲደርሱ አዲስ መንገድ ይጀምራል። የዩኬ የጥገኝነት ስርአት በጣም ከባድ እና በሰዎች እና በቤተሰቦች ላይ ከባድ ጫናን ያሳድራል። ከሚያውቁት ሃገር ውጪ እና አዲስ የሆነ ስርአት ውስጠ ተረጋግቶ መቀመጥ አብዛኛውን ጊዜ በጣም ከባድ ነው። እና በኮሮና ቫይረስ ምክንያት የመጡት ተግዳሮቶች ደግሞ አብረን ከምንሰራቸው ለጥቃት ለተጋለጡ ሰዎች የበለጠ ከባድ ነው። ማረፊያ ቦታ፣ ገንዘብ እና ቴክኖሎጂ ማግኘት በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ ስኮትላንድ ውስጥ ያሉ ጥገኞች ከድህነት እና ከመገለል በላይ የበለጠ ስጋት ውስጥ ናቸው።

ራሳችንን ካገኘንበት ከዚህ በየጊዜው ከሚቀያየር ሁነኔታ ውስጥ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እና ምክር ከመቸውም በላይ አስፈላጊ ነው። የስልክ እና የኦንላይን መገኘታችንን እየጨመርን ነው ይህም የአገልግሎት ተጠቃሚዎቻችን ምግብ፣ መጠለያ፣ ህክምና፣ እገዛ እና መረጃ ማግኘት እንዲችሉ ነው። ይህ ጊዜ ለሁላችንም በጣም አስፈሪ ነው ነገር ግን በእንደዚህ ቀውስ ውስጥ የሰውን በጎነት እናያለን እና ይህን ተግዳሮት አብረን እንደምናልፈው እናምናለን።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### ይህ ዝግ ወቅት የጥገኝነት ጥያቄዬ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል?

በኮሮና ቫይረስ ምክንያት Home Office የጥገኝነት ጥያቄዎች ላይ የተወሰኑ ለውጦችን አድርጓል።

- መጓጓዝ እንዳይኖር እና ከሌላ ሰው ጋር እንዳይገናኙ ለጥገኝነት ጥያቄዎ መመዝገቢያ አዲስ ስርአት እየገነቡ ነው።
- የጥገኝነት ቃለ መጠይቆችን ለጊዜው አቁመዋል እና የጥገኝነት ጥያቄዎችን ለመወሰን እነዚህን ቃለ መጠይቆች በሌላ መንገድ ለማድረግ ሌሎች መንገዶችን እየፈለጉ ነው።
- የጥገኝነት ጥያቄዎን ያልተቀበሉ እንደሆነ ወይም ለጥያቄዎ ተጨማሪ ማስረጃ ከተጠየቁ፣ ከዚህ በፊት ወደ ሊቨርፑል መሄድ ይጠበቅብዎ ነበር። ከዚህ በኋላ ግን ይህን ማድረግ አይጠበቅብዎትም፣ ማቅረብ ያለብዎትን ተጨማሪ ማስረጃ ወደሚከተለው አድራሻ መላክ ይችላሉ፡
  - Further Submissions Unit
  - The Capital Building
  - Old Hall Street
  - Liverpool
  - L3 9PP

ወይም በሚከተለው ኢሜይል ያድርጉ
CSUCE@homeoffice.gov.uk

- የጥገኝነት ድጋፍ ላይ የነበሩ ማባረሮች እና ማቋረጦች ለሶስት ወራት እንዲራዘሙ ተደርጓል።

### የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ ከተደረገ ወይም በቅርብ ጥገኝነት ከተሰጠዎ፣ ከዚህ በፊት አሁን ካሉበት የጥገኝነት መኖሪያ እንዲወጡ ይደረግ ነበር፣ ነገር ግን ሁሉም ማስወጣቶች እስከ ጁን ድረስ ተራዝመዋል። ስለዚህ እንዲወጣ ማሳወቂያ የደረሰው ሰው ካለ፣ መውጣቱ እስከ ጁን ድረስ ተራዝሞለታል። ይህም የጥቅማጥቅም ክፍያ ላይም ተግባራዊ ይደረጋል።

በኮሮና ቫይረስ መዘጋት ወቅት የጥገኝነት ጥያቄ መጠየቅን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በየጊዜው አዳዲስ መረጃ የምናስገባበትን የስኮቲሽ የጥገኝነት ካውንስል ድረገጽ (scottishrefugeecouncil.org.uk) ውስጥ የእኛን Covid19 ግብአቶች ገጽ ይመልከቱ።

እየተቸገሩበት ያለ ምንም ነገር ካለ (ወይም ስለ አንዳንድ ጉዳዮች ወንድማዊ ምክር ከፈለጉ) የእርዳታ የጥሪ መስመራችንን በ 0141 223 7979 ደውለው ከሰራተኛ ጋር ማወራት ይችላሉ።

በተለይ በዚህ ሰአት - ተገለው ወይም ድጋፍ ሳያገኙ መቀመጥ የለብዎትም!

### የምኖረው በጥገኝነት መኖሪያው ውስጥ ነው፣ ይህም ማለት ማህበራዊ መራራቅን መተግበር በጣም ከባድ ነው። ምን ማድረግ አለብኝ?

Home Office የጥገኝነት መኖሪያ ስፍራዎችን በሃገሪቱ ማስፋት ላይ እየተወያየ ሲሆን ይህም ሁሉንም ሰው ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ለማኖር ነው።

በቀረው ጊዜ ራስዎን በደህንነት ለማቆየት NHS የተወሰኑ መመሪያዎች አሉት፡

- እንደ ኩሽና የመሳሰሉ በጋር የመኖሪያ አካባቢዎች በተቻለ መጠን ትንሽ ጊዜ ብቻ ያሳልፉ
- መጸዳጃ ቤት የሚጋሩ ከሆነ፣ የሚነኩትን እያንዳንዱን ስፍራ በደንብ ያጽዱ እና ከጨረሱ በኋላ በዲተርጀንት ያጽዱት (እና ከእርስዎ ጋር አብረው ለሚኖሩ ሰዎች ይህን እንዲያደርጉ ያሳውቁ!)
- መኝታ ቤትዎ ውስጥ መስኮት ካለ በተቻለ መጠን ክፍት ይተውት

በጣም የተጨናነቀ የጥገኝነት መኖሪያ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ይህ ሁሉንም ችግርዎን እንደማይቀርፍ እናውቃለን። ይህንን ምክርም መከተል ሁልጊዜ የማይቻል ወይም ተግባራዊ ማድረግ ከባድ እንደሆነ እንረዳለን።

ጊዜያዊ መኖሪያዎች በተቻለ መጠን ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ የምንችለውን ሁሉ እያደረግን ነው። የሁሉም ጤንነት ዋጋ አለው። የቫይረሱን ስርጭት ለመቀነስ ሁላችንም እርስ በእርስ መደጋገፍ አለብን። ይህንንም ለማድረግ ሁሉም ሰው የጤና መከላከያ እርምጃዎችን ለመተግበር ግብአቶች ያስፈልጉታል። ማንም ወደኋላ መቅረት የለበትም።

## ልጆቼን በቤት ውስጥ ደስተኛ እንዲሆኑ እና እንዲማሩ እንዴት ማድረግ እችላለሁ?

ልጆችን በቤት ስራ ማገዝ፣ የሚያስፈልጋቸውን ግብአቶች በኦንላይን እና በአካል መስጠት፣ እና ሳያስጨንቋቸው ምን እየተፈጠረ እንዳለ እንዲገነዘቡ መርዳት ሊያጋጥምዎ ከሚችሉ ከቤተሰብ ተግዳሮቶች የተወሰኑ ናቸው።

የቋንቋ ተግዳሮት ካለብዎ ወይም አስተማማኝ ኢንተርኔት ከሌለዎ እነዚኦህ ችግሮች የበለጠ ከባድ ይሆናሉ።

ልጅዎን በቤት ስራ ለማገዝ የሚጠቅሙ ጠቃሚ ግብአቶች ለእርስዎ አግኝተናል፡

- BBC Bitesize: ለሚፈለገው እድሜ ተገቢ ስራ ለመምረጥ ቀላል የሆነ። ለሁሉም እድሜ የሚሆን አዳዲስ ኦንላይን ትምህርቶችን መልቀቅ ጀምረዋል!
- Sumdog: ጨዋታ መሰረት ያደረገ ሂሳብ፣ ሰዋሰው እና የቃላት ልምምድ አስተማሪ። በኮሮና ቫይረስ ወቅት በነጻ ማግኘት ይችላሉ።

ቫይረሱን እና መዘጋቱን ለልጅዎ ማስረዳት ከተቸገሩ፣ ይህንን ይሞክሩ Coronavirus: A Book For Children – ምን እየተፈጠረ እንዳለ ለልጅዎ መንገር የሚችሉበት ነጻ መጽሐፍ።

በቤትዎ ያለዎት የኢንተርኔት አጠቃቀም የተወሰነ ከሆነ ወይም የሌለዎት ከሆነ እነዚህን ግብአቶች ማግኘት የማይቻል ይሆናል።

በኢንተርኔት ትምህርትን ማግኘት እንዲችሉ የቻልነውን ያህል ወላጆችን ለመርዳት እየሰራን ነው። በዚህ ላይ እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ እና ጥገኛ ሆነው የጥገኝነት ሂደት ላይ ከሆኑ፣ የእርዳታ የጥሪ መስመራችን ላይ ይደውሉ (0141 248 9799) ወይም ድረገጻችንን (scottishrefugeecouncil.org.uk) በመጎብኘት እንዴት መረዳት እንደሚፈልጉ ከአማካሪ ጋር ያውሩ።

## እንግሊዝኛ አላወራም። ስለ ቫይረሱ የመንግስት አዳዲስ መረጃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

መንግስት እና ሚዲያ ስለኮሮና ቫይረስ አዳዲስ መረጃ፣ እና ምክሮች በየቀኑ እየለቀቁ ነው። ይህንንም በሚረዱት ለእርስዎ መድረሱ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ እንረዳለን።

አለም አቀፍ ሃኪሞች በ 43 ቋንቋ የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ምክር ለህመምተኞች አዘጋጅቷል። ይህ መመሪያ የመንግስት የዘመነ ምክር እና የጤና መረጃን መሰረት ያደረገ ነው።

በተጨማሪም NHS ስለ ኮሮና ቫይረስ እንዲያውቁ የሚያግዝዎ መረጃ ን በአረብኛ፣ በቻይንኛ፣ በማንዳሪን እና በኡርዱ አትሟል። ወደ ተጨማሪ ቋንቋዎች መተርጎም ላይም እየሰሩ ነው።

አዲሱ ስኮትስ ኮኔክት ፎረም በስኮትላንድ ካሉ የማህበረሰብ ቡድኖች የተውጣጣ እና የማህበረሰብ ድጋፍን የሚያበረታታ እና ጠቃሚ መረጃዎችን የሚያጋራ ነው።

እነዚህን ግብአቶች ለመጠቀም ስልክ እና ኢንተርኔት እንደሚያስፈልግዎ እናውቃለን እና ላይኖርዎት ግን ይችላል። በዚህ ላይ እገዛ ከፈለጉ የእርዳታ ጥሪ መስመራችን ላይ ይደውሉ(0141 248 9799) ወይም ድረገጻችንን (scottishrefugeecouncil.org.uk) በመጎብኘት ከአማካሪ ጋር ማውራት ይችላሉ። አጋሮቻችንን ስማርት ስልኮችን፣ ታብሌት እና ላፕቶፖችን እና ቅድመክፍያ ሲም ካርዶችን እንዲለግሱን ጠይቀናቸዋል እና ለሚፈልጉ ሰዎች እናከፋፍላለን።

## እየኖርኩ ያለሁት በቀን £5 እና ራሴን ለይቼ ነው ያለሁት። ቤተሰቤን እያበላሁ እኔ ደግሞ የሚያስፈልገኝን የጤና እርዳታ እንዴት አገኛለሁ?

በጥገኝነት ስርአት ውስጥ ከሆኑ፣ በሳምንት £37.75 ወይም £35.39 ያገኛሉ። በደህና ጊዜ እንኳን በዚህ አይነት ክፍያ ጤነኛ ሆኖ መቆየት በጣም ከባድ ነው፣ እና ግን እንደሚታወቀው አሁን ደህና የሆነ ጊዜ ላይ አይደለንም። ለዚህም ነው ሰዎች ራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን በዚህ ቀውስ ውስጥ የተሻለ ማገዝ እንዲችሉ መንግስት የጥገኝነት እገዛው ላይ በሳምንት የ £20 ጭማሪ እንዲደረግ መንግስት ላይ ጫና እያሳደርን ነው።

አፋጣኝ እገዛ የሚፈልጉ ከሆነ የእርዳታ የጥሪ መስመራችንን በ (0141 248 9799) ደውለው ለድንገተኛ ጊዜ ፈንድ ብቁ እንደሆኑ ያረጋግጡ።

በግላስጎው ውስጥ እንደ Glasgow Mutual Aid, Refuweegee, Kinning Park Complex, and Glasgow Gurdwara ያሉ ምግብ እያከፋፈሉ ያሉ ብዙ ኦንላይን የማህበረሰብ ድጋፍ ቡድኖች እና ድርጅቶች አሉ። ሙሉ ዝርዝሩን ለማግኘት የ Covid19 ግብአት ገጻችንን ወይም አዲሱን ስኮትስ ኮኔክት ፎረምን ይመልከቱ።

# እንዴት መርዳት እንደሚችሉ

**Covid-19 የጥገኛ እገዛ ፈንዳችን ላይ ዛሬ ድጎማ ያድርጉ** ። እያንዳንዱ ሳንቲም በዚህ ወሳኝ ጊዜ ለጥቃት የተጋለጡ ሰዎችን ለመጠበቅ ይረዳናል።

ስማርት ስልክ፣ ላፕቶፕ ወይም ታብሌት መጿጎም የሚችሉ ከሆነ ያግኙን። እኛ በርቀት ሆነን መስራት ብንችልም ሁሉን ጥገኛ ይህን ማድረግ አይችልም። በ Covid-19 ላይ ወሳኝ አገልግሎቶችንና ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ቴክኖሎጂ በጣም ወሳኝ ነው። ትርፍ ስማርት ስልክ፣ ላፕቶፕ ወይም ታብሌት ካለዎት funding@scottishrefugeecouncil.org.uk ላይ ኢሜይል በማድረግ የሚፈልጉ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ጋር እንዲደርሱ እናመቻቻለን።

ስኮቲሽ የጥገኛ ካውንስል ድጋፍ ለመስጠት እና በስኮትላንድ ውስጥ ላሉ ለጥገኞች እና ለጥገኝነት ጠያቂዎች አፋጣኝ እገዛ ለማድረግ እንደመቼውም ቀርጦ እየሰራ ይገኛል፣ እና ይህ አገዛ ዛሬ ከመቼውም በላይ በጣም ወሳኝ ነው።

እናመሰግናለን